# ለ "ኦሮሚያ ሪፑብሊክ" ነፃ አገራዊነት የፈጠራ ታሪክ ማናፈስ

## መግቢያ

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኦሮሞ ተብዬው ብሔረተኛነት አቀንቃኞች አንዱ መሐመድ ሐሰን እ.አ.አ በ2015 ዓ.ም **The Oromos and the Christian Medieval from** 1300-1700 century በሚል ርዕስ የጋላ ጎሣዎች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ ነጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ይኖሩ እንደነበረ አስመስሎ ያዘጋጀው የፈጠራ ድርሰት አስመልክቶ ታሪካዊ ሰንድ በጊዜና በስፍራ ተገናዝቦ ይቀርባል። በሸዋ ክፍለ ሀገር በመንዝና ግሼ አውራጃ መሐል ሜዳ አቅራቢያ በተለምዶ ግራኝ ጉር እየተባለ የሚጠራውን "ጋላ ጉር" ይባላል ብሎ መቀዠበሩ፤ በይፋት አውራጃ ዓለም ሲፈጠር ጀምሮ የጋላ ጎሣዎች መኖራቸውና የቀዎት ወረዳ መጠሪያ ቀዎት የጋልኛ ቃል ነው የሚል ልፈፋው፤ በአዋሽ ወንዝ ሸለቆና በደዋሮ ከሚኖሩት ነዋሪዎች በምርጥ ቀስተኞነታቸው የታወቁትን የማያ ነገድ ከጋላ ጎሣ ወገን እንደነበሩ አስመስሎ ያቀረበው ተረት፤ በደዋሮ ማለትም በምዕራብ ሐረርጌ፣ በወጅ (በዝዋይ አዋሽና ምደረ ጉራጌ)፣ በፈጠጋር፣ በዳሞት (ወለጋ) ወዘተረፈ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ሁሉ የጋላ ጎሣዎች አስቀድመው ይኖሩ ነበር አስመስሎ የሚቀባጥረው የውሸት ጋጋታ የኦነግ ፕሮፓጋንዳ ዘርፍ መሆኑ ይሰመርበታል። እንኳንስ በመሓል አገር በሸዋ፣ በይፋት፣ በደዋሮ፣ በፈጠጋርና በባሌ ይቅርና እስከ ዘይላ በርበረ ሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ድረስ ነባር ነዋሪዎቹ አርጎባዎች፣ የሃርላ ሃድያዎች፣ ወሰኝ ጠባቂ ክርስቲያን ጨዋዎች እንደነበሩ ይተነተናል። የአዳል ወላስማ ሱልጣናት ሴማዊ ቋንቋ አርጎብኛ ተናጋሪዎቹ ከዋና ማዕከላቸው ከይፋት በአጤ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት በ1435ዓ.ም በጦር ሲሸነፉ ሸሽተው ወደ አውሳና ቀጥሎም ሐረርን ማዕከል ማድረጋቸው፤ በሸዋ ቆላማ ስፍራዎች ለምሳሌ ከመተሃራ፣ ከፈንታሌ በአዋሻ ወንዝ ቀኝና ግራ ዳርቻ፣ በደዋሮ (ከጨርጨር እስከ ሐረር ዙሪያ)፣ እስከ ዘይላና ጅጅጋ ድረስ በሚገኘው አካባቢ፣ በአርባጉጉ፣ በጭላሎ፣ በባሌ ጎባ በወረብ ወዘተረፈ ሁሉ ነባር ነዋሪዎች የአርጎባ፣ የሃርላ-ሐድያ እስላሞች እንጂ የጋላ ጎሣዎች እንዳልነበሩ በሰፊው ይገለጻል። የእስልምና ሃይማኖት በአረብ ስርጎ ገብ ነጋዴዎችና ሃይማኖት ሰባኪዎች በተለያዩ ጊዜያት በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ገብተው ሲያስፋፉ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ በይፋትና ሸዋ፣ በሕንድ ውቅያኖስ ጠርፍ በበርበራ፣ በሞቃዲሾ፣ በሞምባሳ፣ በዘይላ፣ በዛንዩባር ወዘተረፈ. የየመን አረብ ነጋዴዎች ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ገብተው ሲሰፍሩ፣ ከአካባቢው ሕዝብ ጋራ ተጋብተው ተዋልደዋል። በሸዋ ከነባሩ ዐማራና ጋፋት ሕዝብ ጋራ የተጋቡት የነ ማክኅዙማ ሱልጣናትን መሥርተው ለኢትዮጵያ አጤ መንግሥት እየገበሩ ሲኖር ቀጥሎም የይፋት ሱልጣናት የዑመር ወላስማ ተወለጆች ሥርወ መንግሥት ተነስቶ የሸዋውን ሱልጣናት በጦር ደምስሶ ንዑስ እስላማዊ ግዛቶችን ሁሉ በአንድነት ከባሌ እስከ እስከ ዘይላ በርበራ ድረስ ሰባት እስላማዊ ግዛቶችን ሲገዙ ለአጤው መንግሥት በዓመት እየገበሩ መቆየታቸው የተረጋገጠ ሲሆን የይፋት እስላሞችና መሪው ወላስማ የመጠሪያ ስማቸውን ያገኙትም ከዐማርኛ ቃል ይፉ መሆኑ፤ ይፋት በእግእዝ ዊፋት፣ ባረብኛ ወፋት እንደሚባል፤ ባማርኛ ይፉ ማለት ግልጥ፣ ስውር፣ ድብቅ ያልሆነ ነገርን ሲገልጽ፤ እስልምና በግልጽ፣ በይፉ ስለተሰበክና ስለተሰራጨ አገሩ ይፋት ተብሏል። የሸዋና የይፋት፣ የደዋሮና የባሌ የወጂ፣ የፈጠጋር ወዘተረፈ ዐማሮች በነኡመር ወላስማ አማካይነት ስለሰለሙ አርጎባ ተብለዋል። አርጎባ ከዘጠንኛው ክፍለ ዘመን ዘመን ወዲህ የይፋት አውራጅ እስላሞች መጠሪያ ትርጉሙም አረብ ገባ ማለት እንደሆነ፤ እስልምና ስለተስፋፋና ይፉ ስለሆነ አገሩ ይፋት፣ ሕዝቡ ደግሞ አርጎባ፣ ገዥው መስፍን ወይም ባላባቱ ወላስማ እንደተባለና የአዳል ሱልጣናት ከሸዋ እስከ ባሌ ሐረር ደረስ ነባር ነዋሪ እንደነበረ ይገለጻል። ያርጎባ ሕዝብ ተውፌት፣ የታሪክ ሰነድ፣ የሥነ ቋንቋ ጥናት፣ የጥንት ቅርስ ፍርስራሽ በያለበት በተለይም በዛሬው አሩሲ አርባጉጉ አውራጅ፣ በጭላሎ፣ በፈንታሌ፣ በአሰቦት፣ በጨርጨር የተራራ ሰንሰለት አስከ ሐረር ዙሪያ ባብሌ ወረዳ ድረስ በያለበት መገኘቱን፤ የግንብ ቤት፣ የመቃብር ሐውልት፣ የቀጣና እርሻ እርከን፣ ባለ ግንብ ቅጥር መንደርና ምሽግ ፍርስራሾች እስከ ዛሬ እንድሚታዩና የጋላ ከረዩ ዘላን መጤ ጎሣዎች በሐቅ የሚመሰክሩት መሆኑ ይቀርባል። የወረሞ ልሂቃን ብሔረተኝነት ፕሮፓጋንዳ ነኾዎቹ የእነ አሰፋ ጀለታ፣ ነጋሦ ጊዳዳ፣ መኩሪያ ቡልቻ፣ መሐመድ ሐሰን ወዘተረፈ ለኦነግ ዓላማ ለኦሮሚያ ምሥረታ ብለው የሚቀባጥሩት ዝባዝንኪ እራሳቸውና ፀረ ኢትዮጵያ ቀጣሪዎቻቸው የፈጠሩትን የውሸት ክምር ይናዳል።

# የታሪክ ብረዛና ቅልበሳ እስከ መቼ?

መሐመድ ሐስን ዶክተር ለመባል በፀረ ኢትዮጵያው እንግሊዛዊው ሪቻርድ ግርንፊልድ ልዩ አማካሪነት አዘጋጅቶ ከአሰራጨ በኋላ በተከታታይ የታሪክ ቅልበሳና ብራዛውን ያኹጎደጉደዋል።

በታሪክና የጎሣ ጥናት ሽፋን በኢትዮጵያ ላይ በገፍ የሚወርደውን የውሸት ውርጅብኝ በተመለከተ መልካሙ ሰው የሚችጋን ዩኒቨርስቲ አሜሪካዊው የታሪክ ምሁር የተከበሩ ፕሮፌሰር ሃሮልድ ማርኪስ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ በማጣመምና በውሸት ዝባዝንኪ ከረጢት በመሙላት የሚካሄደውን ሰፊ ዘመቻና ውንጀላ በግልጽ አጋልጠውታል። እሳቸውም ያለፈው ምን ሃላፊነት በኢትዮጵያ አለው? << Does the past have any authority in Ethiopia >> በሚል ርዕስ ኢትዮጵያን ሪቪው መጽሔት 2(4) (April 1992) እንዲሁም የኢትዮጵያን ታሪክ ማክሰር "The corruption of the Ethiopian history (1992) በተሰኘ ርዕስ በመሐመድ ሐሰን የተዘጋጀውን መጽሐፍ (The Oromo of Ethiopia: AHistory. 1570-1860, 1990) በሚመለከት የሰጡትን አስተያየት ማገናዘብ በጣም አስፈላጊ ነው።

የጋላ ልሂቃን ቅጥ ያጣና ዓይን ያወጣ ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ በቆርጦ ቅጠላ ለተዘጋጀው የውሸት ክምችት አጸፋ ምላሹን የሚሰጡት በጣት የሚቆጠሩት ሐቀኛ የኢትዮጵያ ልጆች ለምሳሌ እንደ ክቡር አቶ ጌታቸው ረዳ፣ ክቡር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ክብር ዶክተር ኃይሌ ላሬቦ (የታሪክ ባለሙያው)፣ ክቡር አቶ ተክሌ የሻው (የታሪክ ባለሙያ)፣ ክብርት ዶክተር አበባ ፈቃደ፣ ክቡር ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴ (ነፍሳቸው ትማር)፤ ክብር ፕሮፌስር አዩ ሞሚና፣ ክቡር ዶክተር አስፋ ነጋሽ ወዘተረፈ. በስተቀር አብዛኛው በፍርሃት ተሸብቧል። ከጠላት ጋራ ወግኖ ይሞዳሞዳል።

አልፎ ተርፎም አገር ወገን ወዳድ አርበኞችን ለማሰናከል፣ ቢቻልማ ኖሮ አፍ ለማዘጋት እንበለ እፍረት ያዳክራል። በፀጉር ስንጠቃ፣ በወሬና አሉባልታ ማናፈስ ተጠምደ ይገኛል። ሆዳሞች በደመና ላይ ትልቅ ፎቅ ቤት ሠርተዋል። ለይስሙላ ኢትዮጵያዊነት ሲቆዝሙና ሲያላዝኑ በታሪካዊ ጠላቶቻችን ርዳታ ትብብር የፓንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ስፍኖ ኢትዮጵያ አገራችን በአእገር በቀል ቅጥረኞች ተላላኪ አስፈጻሚነት ከዓለም ካርታ ላይ ድብዛዋ ሊጠፉ ተቃርቧል።

መሐመድ ሐስን የውሸት ትረካውን ሲቀጥል "ጋሎች ከ13ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ማለትም ከአጤ ይኩኖ አምላክ (1270 እስክ 1285 ዓ.ም) አስቀድሞ በጥንታዊው ሸዋ፣ ባሌ፣ ደዋሮ (ምዕራብ ሐረርጌ) ይኖሩ የነበሩ ነባር ሕዝቦች ናቸው" እያለ ጽፋል። አስገራሚው ነገር በአንደ በኩል የጋላ ልሂቃን ያቢሲኒያ ደብተራዎችና መነኮሳት የጻፉትን ታሪከ ነገሥትና ዜና መዋዕል አንቀበልም እያሉ ለያቹ ለገራቹ አስቸግረዋል። የጋሞ ተወላጅ ታላቁ ሊቅ አባ ባሕርይ ያይን ምሥክር ሆነው በግእዝ ቋንቋ እ.አአ 1593 ዓ.ም መዝግበው ያቆዩትን ከፍተኛ የታሪክ ሰነድ <u>ዜናሁ ለጋላ</u> ለምን ባማርኛ ተተርጉሞ ለሕዝብ ቀረበ ብለው የጋላ ጠባብ ጎሠኝነት አቀንቃኞች ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ቡራ ከረዩ ብለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጦመኛ ነኝ እንዲሉ መሐመድ ሐሰንና ብጤዎቹ የጽሑፍ ታሪካው ሰንድ ከኢትዮጵያ ታሪከ ነገሥትና ዜና መዋዕል ውስጥ ለጋላ ነባር ሕዝብነት ማስረጃ አገኘን እያሉ ይጠቅሳሉ።

በኢትዮጵያ ከግራኝ አሕመድ ወረራ በፊት የተጻፉትና ከጀሃዳዊ ውድመት በዋሻና በደሴት ለጠላት በማይጠቁት ስፍራዎች ተደብቀው የተረፉት መጻሕፍት እጅግ በጣም ጥቂትና ናቸው። በሸዋ ዝዋይ፣ ጉራጌ፤ ተጉለት፣ መንዝ፣ መራቤቴ፣ በጋሞ ብርብር ማርያም፣ በትግሬ፣ በሰሜንና በጌምድር፣ በጎጃም ተራራዎችና ዋሻዎች ውስጥ በመነኮሳቱ ትጋትና ብርታት በስውር ተቀምጠው ከተረፉት የብራና መጻሕፍት በተለይም በ17ኛው ምዕተ ዓመት የጎንደር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በየጊዜው የተቀዱትና የተባዙት መጻሕፍት በአውሮፓ ዋና ዋና ከተሞችና በኢትዮጵያ ገዳማት ውስጥ ይገኛሉ። ጦረኛና ሊቅ የነበሩት አጤ ገላውዴዎስ ግራኝን በዘንጠፉ ደምቢያ ድባቅ መተው የተቃጠሉ አቢያተ ክርስቲያንና ገዳማትን እንደገና እንዲሠሩ፤ የተቃጠሉት መጻሕፍት እንዲተኩ በማስቀዳት፣ አዲስ በመተርጎምና በማጻፍ መጻሕፍት እንዲበዙ አስደርገዋል። አጤ ገላውዴዎስ በወጅ ማለትም በዝዋይና አዋሽ ወንዝ መካከል በምድረ ጉራጌ ዛሬ ሻሸመኔ በሚባለው ዋና ማዕከልና በጭላሎ አምባ ምሽግ በመነሳት ደዋሮን ማለትም የምዕራብ ሐረርጌ ደጋማ ከዋቢ ሸብሌ ወንዝ በመለስ እስካ ታችኛው አዋሽ ሸለቆ ድረስ ባለው አገር ቢፎሌ ሉባ (1546-1554) አዝማችነት ይመራ ከነበረው የጋላ ወራሪ ጋራ ቀጥሎም ከተከታዩ በምቾሌ ሉባ (1554-1562) ከተመራው ወራሪ ጦር በመጨረሻም በመጋቢት 30 ቀን 1559 ዓ.ም ዓርብ በዕለተ ሥቅላት በፈጠጋር ውስጥ ከአዳሉ ወላስማ የግራኝ አሕመድ ተከታይ ኤሚር ኑር ሞጃሂድ ጋራ በተደረገው ጦርነት አጤ ገላውዴዎስ ተገደለዋል።

ኑር መሐመድ ያጤ ገላውዴዎስን ቸቸቦ ይዞ ወደ ሐረር ሲመለስ በምሥራቅ ይፋት ራሳና አዋዲ አጠገብ አዘሎ ኮረብታ አካባቢ በምችሌ ሉባ አዝማችነት ከፍተኛ ዕልቂት ደርሶበታል። ኑር ወደ ሐረር ነፍሴ አውጭኝ ብሎ ከፈረጠጠ በኋላ የሐርር ከተማን ከጋላ ሉባ ደፈጣ ተዋጊ ጦር ለመከላከል የጀጎል ግንብ አጥር አስገንብቷል። ቀጥሎ የነገሡው አጤ ሚናስ የሥስት ጠላቶችን ጥቃት ለመከላከል በፍጹም አልቻለም። በሰሜን ፈላሻና ቱርክ፣፣ በደቡብ ምሥራቅ ከጋላና አዳል ሱልጣናት ጋራ ያላቋረጠ ጦርነት በማድረጉና ድንገት በመሞቱ ምክንያት ያጤው ማዕከላዊ መንግሥት <u>ከሸዋ እንጦጦና የረር ዋና ማዕከሉ</u> አባይ ማዶ ወደ ደንቀዝና ጎንደር ቋሚ መዲና ተዛውሯል።

**ጎንደር** ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የመንፈሳዊውና ትምህርትና ሥነ ጽሑፍ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቷል። ታሪከ ነገሥትና ዜና መዋዕል ተዘጋጅተዋል። በዚህም መሠረት ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ በ1777 ዓ.ም በአጤ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመን ታሪክ ነገሥት በአንድነት ተሰብስቦ እንዲጻፍ አርገዋል። የዚሁ ቅጅ በፈረንሳይ ፓሪስ ከተማ ቤተ መጻሕፍት በ19ኛው ክ.ፍለ ዘመን በነ ሙሴ ሮሽ ዴሪኩር፤ ሞንዶን ጋለ ፓሴብክስክና እንዲሁም ከሌሎቹ በይበልጥ ቁጥራቸው እስከ 234

የሚደርሱትን የብራና ልዩ ልዩ መጻሕፍት በሙሴ ቶማስ አንቷን ዳቢዲ ተወሰደው እሱም ለሳይንስ አካዳሚ ማኅበሩ አበርክቷቸው የፓሪስ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ንብረት ሆነው ያውሮፓ ሊቃውንት መመራመሪያ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል። ፈረንሳዊው ሙሴ ፔሩሾን ዡል ያጤ ላሊባላን፣ ያጤ ዘዓ ያዕቆብን፣ ያጤ አምደ ጽዮንን ወዘተረፈ ዜና መዋዕል በ19ኛው ምዕተ ዓመት አሳትሟል።

በጥንት ዐማርኛ የጦረኛዎቹ የኢትዮጵያ አጤዎች መዝሙር፣ ለነ አጤ አምደ ጽዮን፣ ለአጤ ይስሐቅ፣ ለአጤ ዘርዓ ያዕቆብ፣ ለአጤ ገላውዴዎስ ወዘተረፈ. በየዘመናቸው የተዘመረላቸው ከየገዳማቱ ቤተ መጻሕፍት የተመዘገቡት ሁሉ ተሰብስበው በጎንደር ዘመን ዳግም መጻፋቸው ይታወቃል። ታላቅና ሰመ ገናና ለነበሩት አጤዎች ባማርኛ ቋንቋ የተገጠሙላቸው መዝሙሮች እጅግ ከፍተኛ የታሪክ ሰነዶች ናቸው። ለምሳሌም ለአጤ አምደ ጽዮን በ1335 ዓም. የአዳል ሱልጣናት ለማስገበር ከአራት ወራት በላይ በወሰደው ዘመቻ እጅግ ከፍተኛ ድል ሲቀዳጅ የተገጠመለትን መዝሙር ስንመለከተው ያስገበራቸውን አገሮችና የመሪዎቻቸው ስም ተመዝግቧል።

ሐርበኛ አምደ ጽዮን፣ መላላሽ የወሰን.........

ከወጅ ዜብደናን፣ ከገንዝ ጠጠን፤ ከሃድያ አመኖን፤ ከባሌ አሊን፣ ከደዋሮ ሂደሪን፤ ከፈጠጋር ዜላርድን፤
ከይፋት አምበል አቦከርን፤ ከግድም የዊሰይን፤ ከአንጎት ዣን አሞራን፤ ከአገው ቤት አዣርን፤ ከትግሬ
ነገድ ክርስቶስ ይወረድ፤ ከጎጃም ጀን ክምርን፤ ከጋፋት አወላሞን፤ ከዳሞት ለሚን
ማን ቀርህ ከወሰን ሐርበኛ አምደ ጽዮን መላላሽ የወሰን

በአጤ አምደ ጽዮን መዝመር ሆነ በሌሎቹ ነገሥታት አንድም የጋላ አገርና መሪ አልተጠቀሰም። ለምሳሌ ሱማሌ የሚለው መጠሪያ በአጤ ይስሐቅ መዝሙር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሷል። ጋሎች በኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ነዋሪ ቢሆኑ ኖር እንደ ሱማሌ በተጠቀሱ ነበር። መቸም የሌለ ነገር አይገለጽም። ጋሎች አገራችንን ከወረሩ በኋላ ግን በሰፊው ስለነሱ ተመዝግቧል። ስለሆነም መሐመድ ሐሰን በአጤ አምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ዘሀገረ ጋላ የሚለው ምኞታዊ የፈጠረ ተረት ነው። ፈረንሳዊው ሆነ ጣሊያናዊ ወይም ጀርመናዊ ግእዝ አዋቂ ነኝ ባይ ሁሉ የፈጠሩትን ልብ ወለድ ትርካ የታሪክ ሰንድ ብሎ ያለ ጊዜውና ስፍራው መጥቀስ መዘባረቅ ነው። መታወቅ ያለበት ሐቅ አለ። ይኸውም እንኳን ያውሮፓ ተመራማሪ ተብዬ አወናባጆች ድርሰት ይቅርና በአገር ቤት በጎንደር ዘመን ከተዘጋጁት ውስጥ ያንዳንድ መጻሕፍት ይዘትና ገለጻ ከጊዜና ስፍራ ጋራ ፈጽሞ አይስማማም። ለምሳሌ ታሪከ ነገሥት ስለ አጤ ገላውዴዎስና አጤ ሚናስ ኮተሊክ መሆን የሚተርከው ፍጹም የፈጠራ ወሬ ነው። ከሁሉም በላይ በድርሳነ ራጉኤል ስለ ግራኝና ጋላ ወረራ አጤ ልብነ ድንግል የጋላ አእዋሚ ባሕልን በመከተላቸው ምክንያት እግዚአብሔር ለመቅጣት ግራኝ አሕመድን አስነሳባቸው ተብሎ በስፍራና በጊዜ ያልተያያዘና የማይያዝ በአስራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በኢትዮጵያ በቀደም ተከተል የተፈጸመውን የግራኝ አሕመድና የጋላ ወረራ ታሪክ አስመስለው ለመግለጽ ጸሐፊዎቹ ከጊዜ በኋላ የፈጠሩት መሆኑን ዶክተር ላጵሶ ድሌቦ ያደርጉት ትክክለኛ ግንዛቤ በግልጽ ያስረዳል። (የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ 1982 አዲስ አበባ ገጽ 118)

ስለ ገራኝ አሕመድ ማንነትና ስላደረገው ያ15 ዓመት ጅሃዳዊ የወረራ ጦርነት የኛ ጸሐፊዎች የመዘገቡት እጅግ በጣም ጥቂትነው። ርግጥ ነው ግራኝ አህመድ ለጅሃዱ ጦርነት ከፍተኛ ርዳታ ከአረቦችና ቱርኮች ዘመናዊ መድፍና መድፈኞች በሽህ የሚቆጠሩትን አቅርበውለታል። በታሪክ ነገሥት "ወተንስአ ግራኝ በእግረ ትዕቢት እንዘ ይትአመን በመድፍ ወበቱርክ" በማለት የተመዘገበው ትክክለኛ ነው።

ነገር ግን ከጦርነቱ መልስ የተጻፉት አንዳንዶቹ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ጦርነቱን የእግዚአብሔር መቅሰፍት አስመስለውታል። ስለ ግራኝ የሚተረከው ተውፌትና የተጻፈው ከፊሉ ለሥነ ጽሑፍ የቋንቋ እድገት ምርምር እንጂ የታሪክ ሰንደስ ከቶ አይሆኑም። ጥንታዊ ቁም ድንጋይ ሕውልት ሁሉ ከደቡብ እስከ ስሜን የግራኝ ሥራ እንደሆኑ የሚተረከው ዓይነት ምንም ዋጋ የለውም።

በወረራው ወቅት በይፋት በአንጾኪያና አይፈር የጦር ሜዳ በወርሃ የካቲት 1524 ዓም ጀግናው የባሌ ሠራዊት በራስ አስላም ሰገድ አዝማችነት የተሸነፈው በግራኝ የመድፍ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ሸሃብዲን አብድልቃድር (አረብ ፋቂ) የአጤ ልብነ ድንግል ሠራዊት እንዴት እንደተሸነፈ በከፍተኛ ትጋትና ሰፊ ሐተታ ከጅሃዳዊ ዕይታው አንጻር የጦርነቱን ዜና መዋዕል በሰፊው መዝግቦታል። ዳሩ ግን በአረብ ፋቂ የተመዘገቡት የቦታና የነገድ ስሞች በጦርነቱ ወቅት ትልቅ ሚና የነበራቸውን ለምሳሌ በዝቋላ አጠገብ እንደሚገኘው ሽምብራ ኩሬ፣ በይፋት አንጾኪያ፣ አይፈር፣ ወሲል፣ ወዘተረፈ የመሳሰሉትን ዛሬ በትክክል ለይቶ ለማመልከት አይቻልም። በቃል መመሳሰልና ይሆናል መላምት ብቻ ለምሳሌ ይፋ የሚለው ያማርኛ ቃል ኢፋ ከሚለው የጋልኛ ቃል ትርጉሙ ብርሃን ከሆነው ቃል ጋራ በማመሳሰል ብቻ የጋላ ጎሣ በሸዋ ምድር በይፋት፣

በወጅ፣ በደዋሮ፣ በየጁ ወዘተረፈ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ለመኖሩ ማስረጃ ነው እያሉ የጋላ ልሂቃን የሚተርኩት ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። ከዚህም ሌላ የግራኝ አሕመድን ዜና መዋዕል ጸሐፊው አብድልቃድር አረብ ፋቂ አጁ ወይም አል አጁ የሚል መዝግቧል ይህም የጁ ማለት ነው እያሉ በቤተ ዐማራና አንጎት ከጋላ ወረራ በኋላ ዛሬ ወሎ በሚባለው አገር ከግራኝ በፊት የወሎ ጋሎች በዚያው የሚኖሩ ነባር ሕዝብ እንድሆኑ ተደርጎ የሚነዛው በሬው ላም ወለደ ነው።

በግራኝ አሕመድ ወረራ ማግስት ያይን ምስክሮች እነ በርሙደስ በደዋሮ የተደረገውን የጋላ ወረራ በወቅቱና በስፍራው መዝግበውታል። በአጠቃላይ የጋላ ጎሣዎች ከ1537ዓ.ም በፊት በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ውስጥ <u>አንድም የጋላ ጎሣ</u> በጭራሽ ይኖር አልነበረም።

**ባሊ** በግእዝ መጽሕፍት ባማርኛ ባሌ ከሰባቱ እስላማዊ የአዳል ዝይላ አካባቢ የአጤው ገባር ግዛት አንዱ እንደነበር ዕውቅ የዘመኑ የዓረብ ሊቃውንት እነ ኦልማሪና ማቅሪዚ የመዘገቡት፣ ከአጤ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በባሊ ወሰን ጠባቂ ክርስቲያን ጨዋዎች ሰፍረዋል። የአርጎባ፣ የሃርላ ሃድያ እስላሞችና ያማራና የጉራጌ ልዩ ልዩ ጎሣዎች መኖሪያ ነበሩ። በባሌ ከጥንት ክርስቲያን ነዋሪዎች የፋሲልና ፈንከል ነገድ ያማራ ዘርያዎች መሆናቸው ይታወቃል። ያባ አናሪዎስ ታላቅ ገዳም በባሌ ወረብ ከጋላ ወረራ በፊት መኖሩ ይታወቃል። በባሌ ጎባ አጠገብ የፋሲል ተራራ ሲባል የቆየውን ጥንታዊ ስሙን የለውጠው ደርግና መኢሶን ናቸው።

**የሃድያ** እስላማዊ ግዛት እስከ መቃዲሾ ጠርፍ እንደሚደርስ ታዋቂው የጅኦግራፊ ምሁር ባልተር ተለዝ ያይን ምስክሮች እነ ሎቦ፣ አልሜዳን፣ ፍራንሲስኮ አልቫሬዝን ወዘተረፈ የሰጡትን መረጃ መሠረት በማድረግ በ1560 ዓም ያዘጋጀው መጽሐፍ ያረጋግጣል።

**ደዋሮ** የምዕራብ ሐርጌ ደጋማ አካባቢ ከአዋሽ ወንዝ በመለስ ከባሌ ጋራ በዋቢ ወንዝ የሚዋስነው፣ ከይፋትና ፈጠጋር ጋራም አጎራባች አገር በሆነው ውስጥ ነበር ነዋሪዎች፣ ዐማሮች፣ አርጎቦች፣ የሃርላ-ሃድያዎች፣ ጉራጌዎች፣ ማያዎች ወዘተረፈ እንጂ አንድም የጋላ ጎሣ አልነበረበትም።
ስለ ጋላ ነገድ የተደረጉትን ምርምሮችን በሁለት ክፍል ለይቶ ማቅረብ ይቻላል።

**፩ኛ፣** የመጀመሪያው ጥናት የሚያመለክተው እነዚህ ዘለን ጎሣዎች ከጥንታዊ ሰሜን ሱማሊያ ሀርጌሳና በርበራ አካባቢ መኖሪያቸው ያለማቋረጥ በሱማሌ እስላማዊ ጎሣዎች ስለተባረሩ ወደ ደቡብ ምዕራብ በሸበሌና ጅባ ወንዝ መካከል ከቤናድር የታችኛው ሸበሌ ሸለቆ ፍልሰው ሲኖሩ አሁንም በድጋሚ በሱማሌ ጎሣዎች ሲባረሩ እስከ ቱርካና ሐይቅ አካባቢ ቆይተው በስተሰሜን አቅጣጭያ ተጉዘው በሲዳሞ ቦረና በኩል የገናሌ ወንዝን ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ግዛት ባሌ ክፍለ ሀገር በ1537 ዓም እንደገቡ ነው።
ጋሎች በሰሜን ሱማሊያ ለመኖራቸው የሱማሌ ጎሣ መሪዎች ይተርካሉ። እንግሊዛዊው ኤም.ልዊስና ጣሊያናዊ ኢንሪኮ ችሩሊ ያደረጉት ጥናትም ሱሜሌዎች ከሚሉት ትረካ ጋራ ይስማማል።
ከዚህም ሌላ በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈው የምሥራቅ አፍሪቃ ጠረፍ ሱልጣናት ዋስዋሂል ሕዝብ ዜና መዋዕል <u>አል ኪታብ አል ዛንጂ</u> (የጥቁሮች መጽሐፍ) ጋሎች ከየመን መጥተው በጁባ ወንዝና ቤናዲር ኪስማዩ ሲኖሩ በሱማሌዎች መባረራቸውን፤ ሰው ገድለው እንደሚሰልቡ፣ ካሹ ከሚባሉት ገበሬ ነባር ነገዶች ጋራ በዛሬ ምሥራቅ ኬንያ በታና ወንዝ ሸለቆ ዘወትር በውጊያ ላይ እንድነበሩ በሰፊው ተመዝግቧል።

**፪ኛ.** የጋሎች መነሻ አገር ከቪክቶሪያ ሐይቅ ኒያንዛ በስተምሥራቅ አካባባቢ ነው። ኬኒያ ተራራ አጠገብ የኖሩ የነበሩት ጋሎች በየጊዜው ወደ ተራራው እየሄዱ እናታቸው እንደሆነ ሁሉ መስዋዕት ያቀርባሉ። ያለው እሳቦት በምሥራቅ አፍሪቃ ኬኒያን የምድር ሰቅ አካባቢ በ15ኛው ክ.ፍለ ዘመን በተከሰት እሳት ገሞራ ምክንያት ሰዎች ወደ ተለያዩ አቅጣቻዎች ተሰራጭተዋል። Among the southern Galla tradition appears to be mainly concerned with expulsion of the race from the country now occupied by the Somali. Their original home was posibly in the district east of Victoria Nyanza, for the tribes near mount Kenya are stated to go on personal pilgrimages to the mountain making offerings to it as if it to their mother. A theory has been advanced that the grea exodous which it seems certain took place among the peoples throughout eastern Africa during the 15th century was caused by some eruption of Kenya and other volcanos of equatorial Africa. ( Encyclopedia Britanica, Volume XI 1910 , PP.413- 414)
ጋሎችም በምዕራብ ኬኒያና ምስራቅ ዩጋንዳ ከዚያም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንደተሠራጩ፣ ከአባያውያን ጎሦች ጋራ በአደረጉት ግንኙነት ምክንያት በወንድ የእድሜ ፆታ መለያ ቡድን ማኅበረሰባዊ አደረጃጀትን እንደወረሱ ይገመታል።

የጋላ ነገድ ከአፍሪቃ መሓል የመጣ ነው የሚባለውም ትክክል ነው። በሰሜን ታንዛንያና ታላላቅ ሕይቆች አካባቢ የሚኖሩ ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ምቡሉ ወይም ኢራቅው የተባሉት ጎሣዎችም ይገኛሉ። የኬኒያ ምድር ቀዳሚ ነዋሪዎች አዳኝና ፍራፍሬ ለቃሚ የዱር ሰዎች (Bushmen) በማስለቀቅ የሰፈሩት ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ። ባንቱዎች ከበስተምዕራብ መጥተው ሲሰፍሩ ኩሻውያኑ ወደ ሰሜንና ደቡብ ተንቀሳቅሰዋል። ያልተሰደዱት እስከዛሬ በመጤው ባንቱና አባያውያን ጎሣዎች ዘንድ በጥቅል ዶሮቦ በመባል ተለይተው ይታወቃሉ። ዶሮቦዎች በኬኒያ ተራራ ዙሪያ ሲኖሩ በኪኪዩ ባንቱ ሰፋሪዎች ተፈናቅለዋል።

ጋሎች ከቆላማው የሸበሌና ጁባ ወንዞች መካከል ቤናዴድር መኖሪያቸው በሱማሌ ዘላኖች ሲባረሩ ወድ ቱርካና ሕይቅ አካባቢ ሸሽተው ከቆዩ በኋላ ነው ወደ ሰሜን በማቅናት በ1537 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለመግባት አመቺውን ሁኔታ የፈጠረላቸውም በክርስቲያኑ የኢትዮጵያ አጤ መንግሥትና በግራኝ አሕመድ የቱርክና አረብ ቅጥረኛ መካከል በተደረገው የ15 ዓመታት ጅሃዳዊ ዕልቂት ወረራና ዝርፊያ የባሌ ገበሬ ነዋሪ ሕዝብ ወሰን ጠባቂው ጨዋ በማለቁና ለባርነት በመሸጡ ነው።

ከዚህም ሌላ ከአጤው የግንባር ተዋጊ ጨዋ ሠራዊት ይልቅ ተከታታይ የጋላ ዘላን የሉባ የደፈጣ ውጊያና ዘረፋ የላቀና የተሰማማ ስልት በመሆኑ በሰፊው ተስፋፍቶ ለመስፈር አስችሏቸዋል። በየስምንት ዓመቱ ያላቋረጠ ወረራና ዝርፊያ በማድረግ ነው ከደቡብ ባሌ አስከ ሰሜን ትግሬ፣ ከምሥራቅ ደዋሮ ዘይላ እስክ ምዕራብ ቢዛሞ ወይም ወለጋ ድረስ ባለው ለም ምድር ላይ ተንሰራፍቶ ለመስፈር እንደበቁ የወረራውና ዝርፊያው ሰለባ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ጠመንኹ ራሱ መቶ ራሱ ይጮሃል እንዲሉ የጋለ ልሂቃንና ነፃ አውጭ ኦነግ ተብዬው የቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮች ድርጅት ለ"ኦሮሚያ" መንግሥት ምሥረታ አዲስ የፈጠራ የውሸት ታሪክ ማስረጨትና ፀረ ዐማራ የጥላቻ ቅስቀሳ መንዛት ሥራቸው ቢሆንም ያሰቡት አይሳካም። የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ታሪክ የመቶ ዓመት ብቻ ነው ብለው ሲንደከደኩ ቆይተዋል።

አሁን ደግሞ የጋላ ታሪክ ከዛጉዌ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እንዲያውም ከአጤ ይኩኖ አምላክ ሥርዎ መንግሥት ጎን ለጎን ባልታወቀ ስፍራ አሸሞንሙነው አስቀምጥውታል። ዘወትር የሚያነብንቡት አበሻዎች በአጤ ምኒልክ መሪነት የኦሮሞዎችን ጥንታዊ የገዳ ሪፑብሊክ በጉልበት ወረው ቅኝግዛት አድርገዋል፤ የገዳ "ዴሞክራሲያዊ" ሥርዓትን "አቢሲኒያውን" አጠፉት፣ ወዘተረፈ ብለው ይወሻክታሉ። በተቃራኒው የጋላ ጎሣዎች በሉባ ደፈጣ ውጊያ እየሰለቡና እየዘረፉ በኢትዮጵያ ምደር መስፈራቸው ቅኝገዥነት አይደለም። የጋላ ወራሪ አረመኔያዊ ጭፍጨፋን "ኦሮሞ" በመባል ከታሪክ የሚፋቅና የሚረሳ እየመሰላቸው በከንቱ እነደ ቀጥር እባብ ይቅነዘነዛሉ። ሌላው ትልቅ ማወናበጃ "አቢሲኒያ በአውሮፓ ኤምፔሪያሊስቶች ርዳታና ፈቃድ በአፍሪቃ ቅርምት ወቅት የተመሠረተች አገር ናት" እያሉ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ይዘላብዳሉ። በነሱ ዕይታ የአድዋው ጦርነትም ሽርሽር ነበር። የጉንዲት፣ የመተማ፣ የአምስት ዓመቱ ፀረ ፋሽስትና ፀረ ቅኝግዛት ትግልና መስዋእትነት ወዘተረፈ ሁሉ የሉም። በጋላና ሱማሌ ቅጥረኞች እሳቦት ደቡብና ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት የኢትይጵያ መንግሥት ግዛት አካል ሆነውም አያውቁም። ያበሻ ንጉሥ አጤ ምንሊክ ልክ እንድ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ እስፓኝ፣ ኦስማን ቱርክ ወዘተረፈ ቅኝገዥ ተስፋፊዎች ኦሮሚያንና ሱማሊያን ቅኝግዛት አደረገብን እያሉ ያናፋሉ።

# ያውሮፓ የጎሣ አጥኝ ተብዬዎቹ ታላቅ ሴራ

አፈ ታሪክ ወይም ተውፌት ለጽሑፍየለሽ ማኅበረሰቦች ለታሪክ ማስረጃነት ያለውን የተወሰነ ልክና ገደቡን አልፈው ለኦሮሞ ብሔራዊ ማንነት ለመፍጠር ታስቦ ፈረንጅ ጌቶቻቸው ከጀርመን፣ ከጣሊያንና እንግሊዝ የለየላቸው ፀረ ሴማውያን ርዝራዦች በጎሣ ጥናትና በታሪክ ሽፋን ከፋፋይ ተረት ተረት እየለቃቀሙ፣ የኢትዮጵያን ጥቁር ሕዝብ ለአያሌ ሺህ ዘመናት በነፃነት መኖሩና የፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፋሽስት ተጋድሎው ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ትግል መሪ ኮከብ መሆኑ የውስጥ እግር አሳት የሆነባቸው ፀረ ጥቅር ዘረኞች በጥላቻና ንቀት እብሪት ስሜት ተወጣጥረው ያላጠናቀሩት በሬው ላም ወለድ የጎሣ ጥናትና የውሸት ታሪክ፣ና ያማራ ሕዝብ ጥላቻ ቅስቀሳ የለም። የሻዕቢያ ቅጥረኞች ምድረ ባሕር የኢትዮጵያ አካል ሆናም አያውቅ፣ ኤርትራ አረባዊት ናት፣ የሃይማኖትም ሆነ የታሪክ ምንም ዓይነት ግንኙነት የለም እያሉ ሲደናበሩ እንደነበረው ኦነግና ልሂቃኑ ሁሉ የተጋቱትን ፀረ ኢትዮጵያ ስብከትና ያማራ ጥላቻ ቅስቀሳ ያስተጋባሉ። የኢትዮጵያን ሕዝብ በባንቱስታ አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ  ልክ እንደ ወራሪው ፋሽት ጣሊያን ርስ በርስ በማቃረን ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ላይ ለማጥፋት ቋምጠዋል። በወያኔ ትግሬ ቅጥረኛነት የጎሣ ክልል እስርቤት ሕዝቡ በያለበት ይተራመሳል።

ጀርመናውያን እነ አይከ ሃበርላንድ ስለ ጋላ፣ ኡልሪህ ባራውኬምፌር ስለ ሃድያ፣ ሄልሙት ሽትራውብ ስለ ኦሞዊ

ነገዶች በደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ ቆይተው ልዩ ልዩ ተውፊት ሰብስብን ብለው "ታሪክ" ጽፈዋል። ሃበርላንድ ጋላ ደቡብ ኢትዮጵያ የተሰኛ መጽሐፍ ከአዘጋጀ ባኋላ የአፍሪቃ አጠቃላይ ታሪክ ቅጽ 5 ተባባሪ አዘጋጅ በመሆን ሠርቷል። ስለጋሎች ጥንታዊ መነሻ፣ አገርና ባሕል አዲስ ግኝት ፈጠርኩ ብሎ አትቷል። የፈጠረው አዲስ ታሪክ የኢትዮጵያን ጥንታዊ አገርነት ለመበታተን በጥንቃቄ የተዘጋጅ፣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በተረት ተረት፣ ባማራ ሕዝብ ጥላቻና ከፋፋይ የጎሣ ጥላቻ ቅስቀሳ የተሞላ ለመሆኑ እራሱን ከዘረኝነት እይታ ላጸዳው አስተዋይ ሕሊና ያለው ሁሉ ይገነዘባዋል። ብራውኬምፐር ስለ ሃድያና እስላም በኢትዮጵያ ብሎ በጻፈው የጎሠኝነት መቀስቀሻ ድርሰት ዛሬ በኢትዮጵያ ለሰፈነው የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ማመሳቃቀል አስቀድሞ የዘራው በዘመነ ወያኔትግሬ የጎሣ ፖለቲካ ፍሬ አፍርቶለት በሕይወት ዘመኑ እያጨደ በመሆኑ የተሰማውን ደስታ በአለፈው ዓመት ገልጿል። በርሱ ተረት ተረት ምክንያት ነው ስልጤዎች ከሐረርጌ ጨርጨር የመጣን አደሬዎች ነን፤ ጉራጌ አይደለንም ብለው የተገነጠሉት።

በአጠቃላይ የወያኔ ትግሬና ተለጣፊዎች የወረሞ፣ የሲዳማና ሌሎች ነገዶች በአውሮፓ የጎሣ አጥኝ ተብዬዎቹ በነብራውኬምፐርና አይከ ሃብርላንድ፣ ባክስተር፣ ማርካኪስ፣ አሌክሳንድሮ፣ ወዘተረፈ ፀረ-ኢትዮጵያ ሴረኞች ተቀንባብሮ በተነዛላቸው ያማራ ሕዝብ ብቻ ገዥነት፣ ጨቋኝነት፣ ቅኝገዥነትና፣ ነፍጠኛነት፣ ትምክህተኛነት፣ ተስፋፊነት ቅስቀሳ፣ና ስብከት ያስከተለው ውጤት በያለበት ዐማራውን የጎሣ ማጽዳትና ማጥፋት ይላማ መሆን ነው።።

ያውሮፓ ዘረኞችን ሴራ በተመለከተ ታላቁ የሴኒጋል ተወላጅ ሼይክ አንታ ዲዩጵ የጥንት ግብፅ መሠረቷ በተሰኘው ጥናታቸው ሲይስገነዝቡ፣

<<ዛሬ ራሳቸውን ምዕራባዊ ባይ ለራሳቸው ማኅበረስብ ብሔራዊ አንድነት ዋጋ ሲሰጡና ሲጠነቀቁ፣ ከፋፋይ መላምትን ከራሳቸው ማኅበረሰብ ሲያስወግዱ፤ ነገር ግን ሳያስቡት ይሁን ሆን ብለው አሮጌውን ከፋፋይ ዘዴ አውሮፓዊ ባልሆነው ኅብረተስብ ላይ ይጠቀሙበታል።>> ብለዋል።

<< occidentals who value their national cohesion are carefull to avoid examinig their own sociteis on so divisive a hypothsis but continue unthinkgly to appply the old methods to non- European societies. >> (Origin of ancient Egyptians, Africa today p.145)

ስለሆነም እነ ሄልሙት ሽትራውበ፣ ኤሪካ ሃብርላንድ፣ ብራውኬምፐር ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ የጻፉትን ከፋፋይና ዘረኛ ድርሰት በአጭሩ ማቅረብ ግድ ይላል።

ሽትራውበ ሻንቅላ፣ ጋሞ ወዘተረፈ ለመሳሰሉት ቃላት አመጣጥ ሲጽፍ ጋሞ የተባለው ቃል ኦሞዊ ጎንጋ ቃል ሳይሆን ዐማሮች ሆርሰት ተራራ አካባቢ ለሚኖረው ነባር ሕዝብ መጠሪያ ያወጡት ነው፣ ቃሉም ገማ ከሚለው ቃል ሲሆን ይህም በጣም መጥፎ ስድብ ነው። (H.Straube, Westkuschihitische Völker-Süd-Äthiopien Stuttgart , 1963, p.142) እያለ ጋሞ ባገሬው ሕዝብ ጋሞኛ ቋንቋ አንበሳ ማለት መሆኑን ሸፍጦ ምንም ግንኙነት ከድምጽ አወጣጡ በስተቀር ከሌለው ገማ ጋራ አመሳስሎ የራሱን ኅብረስተስብ ቀንደኛ ዘረኛነት፣ ፀረ ጥቁርነት፣ ፀረ ሴማዊነት፣ በንቀትና ጥላቻ የሚሉትን ትርጉሜ በቀጥታ አቅርቧል። ያማራ ጥላቻ ለመንዛት ለመቀስቀስ ታስቦ እንጂ ባማርኛ ሻንቅላ ፈጽሞ ስድብ አይደለም። ሸነቀለ ማለት ቀዳው የጠቆረ ከተባለው ቃል ይወጣል።ሻንቅላ የነገድ ስም ገላው በፀሐይ ሙቀት የጠቆረ ተብሎ ባማርኛ መዝገብ ቃላት ተመዝግቧል።

ሃበርላንድ ስለ ጋላ በሰብሰበው ተውፌት ጋላ የተባለው መጠሪያ ያማሮች ፈጠራና ስድብ ነው እያለ ሐሰት ጽፏል። ዳሩ ግን ባማርኛ ጋላ የነገድ መጠሪያ ስም በኢትዮጵያ በዝቶ የሚገኝ ሕዝብ ተብሎ ሲጻፍ ስድብነቱ ከምኑ ላይ ነው? እርግጥ ነው ሁለተኛው የጋላ ትርጉም ክርስትና ያልተነሳ፣ ያልተገረዘ፣ ያልተጠመቀ፣ እስላም ወይም ይሁዲ ያልሆነ አሕዛብ አእዋሚ ማለት ነበር። ይህም ሐቅ ነው። ጋሎች በመጀመሪያ ክርስቲያኖች ወይም አስላሞች አልነበሩምና። ለእባብ፣ ለዛፍ፣ ለውሃ ያመልኩ ነበር።

ኋላ የመጣ ዓይን አወጣ፣ እንዲሉ የጀርመን፣ የስዊድንና የእንግሊዝ ወዘተረፈ ጠረ ማርያም ክርስቲያን ተብዬዎች እንደ ጋላ አረመኔዎች የነበሩት ለኦርቶዶክሳውያን ለኢትዮጵያና ለግሪክ ክርስትና ለመስበክ ተንጠራርተው ከሽፈባቸዋል።።።

ያውሮፓ አሕዛብ ኦሪትን ያልተቀበሉት ለጨረቃ፣ ለድንጋይ፣ ለዛፍ፣ ለውሃ ጣዖት አምላኪዎች የነበሩት ሁሉ በጣም ዝግይተው ነው በወንጌል ሕዲስ ኪዳን እምነናል ያሉት። ክርስቲያን ነን ብለውም እንኳን ዋና ባሪያ ነጋዴና ነባር ሕዝቦችን በአሜሪካ፤ በአውስትራሊያና በያለበት ሲጨፈጭፉ የነበሩ ናቸው። በኢትዮጵያ ባሪያ ነጋዴዎች እስላም ጀበርቴዎች፣ ሱማሌዎችና አረቦች እንጂ ክርስቲያን አበሾች አልነበሩም። በፍትሐ ነገሥት የባሪያ ንግድ የተከለከለ ስለነበር ክርስቲያን ሆኖ ባሪያ የሚነግድ በስቅላት ይቀጣል።

በታወቀው ያውሮፓ ዘረኞች መከፋፈያ ስልት ፀረ ዐማራ ስብከት ለማራገብ ታስቦ ነው እንጂ ጋሎችንማ አረመኔ (heathen) አእዋሚ ብሎ በሸዋ ቆይታው (1839-1842) የጻፈው፣ ልዩ ትኩረት አድርጎም በእግዚአብሔር ፀጋ ፕሮቴስታንት ተብዬውን ከተቀበሉ በኃላ ጌታ ባውሮፓ ለጀርመኖች ላሳየው ተልዕኮ መሳካት የተመረጡ

እንደሚሆኑ የተመኘው ጀርመናዊው የሃን ክራፍ የእንግሊዝ ሚሲዮን ቅጥረኛ አልነበረም?
ክራፍ ወደ ሸዋ ዳግመኛ እንዳይገባ ስለ ተከለከለ፣ ከሰሜን ኢትዮጵያም ስለተባረረ ያደረበት ያበሻ ሕዝብ ክርስቲያን ጥላቻ ከፍተኛ ነበር። ክራፍ ከሸዋ በስተደቡብ ያሉት ጋሎች የእስላሞችን መስፋፋት ሊመክቱ የሚችሉ፣ የአፍሪቃ ጀርመኖች ሊሆኑ ይችላሉ ካለ በኋላ ጋሎች እራሳቸውን ኦርማ፣ ወይም ኦሮማ፣ ቋንቋቸውንም አፋን ኦርማ ስለሚሉ፣ ለራሳቸውና ለሚኖሩበት አጠቃላይ መጠሪያ ስሌለቸው ኦርማኒያ ተብለው እንዲጠሩ ሃሳብ አቀረበ። የጋሊኛ ቋንቋ ምሁር የነበሩት ካርል ቱትሼክ ጋሎች ስማቸውን ያገኙት ከራሳቸው ቋንቋ ገላ ነው። አበሾችም ሆኑ አረቦች አልሰጧቸውም በማለት ተቃውመውታል።
ሌላው የቋንቋ ሊቅ ሊዎ ራይነሽ የተባለው ደግሞ ጋላ ከሱማልኛ ቃል ጋል፣ ጋሎ ማለትም እንግዳ፣ እስላም ያልሆነ፣ አረመኔ፣ አእዋሚ ማለት እንደሆነ እ.አ.አ በ1902 ዓ.ም ባዘጋጀው የሱማልኛ መዝገበ ቃላት ያረጋግጣል።
እነ ሃበርላንድ ለዩሃን ክራፍና ብጤዎቹ እቅድና ምኞት መሳካት በጥንቃቄ ያጠናቀረው ተረት ለኦሮሞ ብሔረተኛነትስሜት መቀስቀሻነት ታቅዶ ስለ ጋላ ጎሣ የላቀ ወታደራዊ ድርጅት፣ የገዳ ሥርዓት፣ ዴሞክራሲ፣ የዶማ ገበሬነት፣ ወዘተረፈ ሽንገላ ለመጻፍ ስለምን ኢትዮጵያዊ ዐማራውን ሕዝብ ለይቶ የከፋፋይ ቅስቀሳ መርዙን ርጭቷል። ዝባዘባዝንኪ ትረካውን ሲነዛ፣
"ከዐማሮችና አውሮፓውያን ጸሐፊዎች ከእውነት የራቀ ገለጻ ማለትም ጋሎች የፈለሱት ከማዳጋስካር በጥምባሳ በኩል፣ ወይም ከሰሜን ሱማሊያ እንድሚሉት ሳይሆን ኦሮሞች እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ይህም የሚረጋገጠው ከጠቅላላው ባሕላቸውና ልምዳቸው ነው። ከዛሬው ባሌ ክፍለ ሀገር አካባቢዎች በመነሳት ወደ ኢትዮጵያ መሃል ደጋዎችና በስተደቡብ በዛሬዋ ኬኒያና ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ትልቁን ፍልሰታቸውን ያከናወኑት።" (የአፍሪቃ አጠቃላይ ታሪክ ቅጽ 5 ገጽ 716)
ጋሎች ከየትም ማለትም፣ ከአውስትራሊያ፣ ከማዳጋስካር፣ ከእሲያ፣ ከየመን፣ ከማዕከላዊ አፍሪቃ ወዘተረፈ ፈለሱ ቢባል ሐቁን አይለውጠውም። ከ1537 ዓም በፊት በኢትጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ ነባር ዜጋ አልነበሩምና። ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሐቅ በ16ኛው ምዕተ ዓመት የግራኝ አሕመድ ወረራ የከፈተላቸውን በር ተጠቅመው በበሌ በኩል ገብተው በተከታታይ ወረራ ተስፋፍተው መኖር ከጀመሩበት ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ኢትዮጵያዊ አልሆኑም አልተባለም። ጋላ አገራችንን ከመውረሩ በፊት እውነተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ማላት ግን ሆን ተብሎ ለማወናበድ የተቀመረ ነው። እውነተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመሆናቸው ማረጋገጭያ የተባለው የፈጠራ ምኞት ፍጹም ባዶ በተለይም ባማራ ጥላቻ ብቻ የተቀመረ መሆኑ በግልጽ ይታያል። ሃብርላንድ ፀረ ዐማራ ቅስቀሳውን ሲቀጥል፣
"ሌላው ስሕተት ደግሞ ኦሮሞችን አረመኔ፣ ወይም አራዊት፣ ኋላቀር ከብት አርቢ ማድረጉ ነው። ይህም ከኩሩ ዐማራ የታሪክ ጽሐፊዎችና ባጠቃላይም ዐማሮች ኦሮሞን አሕዛብ፣ ክርስቲያን ያልሆነ፣ እስላም ያልሆነ የላቀ ኅብረተሰባዊ ደረጃ የሌለው፣ ፊደልና ንጉሥ የሌለው አድርጎ በመግለጽ ነው። (ያው)
/ Equally erroneoues are the descriptions of the Oromo as barbarians (savages) or primitive cattle-raisers. These originated from proud Amharic historians and the Amhara generally, who described the Oromos as barbarians, non christians( and also non Muslims), with no sphpstcated social strata, no script and no monarchy. These false estimation of the Oromo as primitive cattle-raiser with no farming skills derives from their cattle complex. ( ibid) /

እዚህ ላይ ሃበርላንድ ለከፋፋይ ቅስቀሳው በጥንቃቄ መርጦ ያቀረበው ቃል ባርባሪክ የተሰኘው ነው። የቃሉ አጠቃቀም ስላልገባው ሳይሆን ሆን ብሎ ያደረገው ስለሆነ የራሱን የጀርመን ሕዝብ ታሪክና ማንነት ማሳሰብ ግድ ይላል። የጥንት ግሪካውያን ሥልጣኔን ከአፍሪቃ አባይ ሸለቆና ከምሥራቅ ባቢሎን የቀዱት ሄሌናውያን ያልሆኑትን በተለይም የጽርዕ ቋንቋ የማይናገሩት ሁሉ በጠቅላላ ባርባሮይ ብለው ይጠሯቸው ነበር። ባርባሮይ የተባለውን ቃል ግሪኮች የተዋሱት ከጥንት ባቢሎንና ሱማርራውያን ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም ባዕድ፣ የውጭ አገር ሰው ማለት ነው። የግሪክን ባሕልና ሥልጣኔ የወረሱት ሮማውያን ቃሉን ወርሰውት ከግዛታቸው በስተሰሜን ለሚገኙት ሥልጣኔየለሽ መደዴ የጀርመን ዘርያ አርመኔ ዘላኖች ልዩ መጠሪያ እንደ ነበር ሮማዊው ዕውቁ የታሪክ ጸሐፊ ታሲቱስ በ98 ዓ.ም የጻፈው ታሪክ ያስረዳናል።
የሮማ ቄሳራዊ መንግሥትና ግዛት በ፭ኛው ምዕተ ዓመት በጀርመን ዘርያ መደዴ (Vandals) ዘላኖች ተወሮ እንደወደመ ይታወቃል።
ለመሆኑ ስህተቱ ከቶ የት ላይ ነው? ጋሎች በ16ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ዘላኖች እንጂ ገበሬዎች እንደ ዐማራ፣ ጉራጌ፣ አርጎባ፣ ከምባታ፣ የም፣ ወላሞ፣ አገው፣ ትግሬ፣ ዐማሮ፣ ከፋ፣ ቦሻ፣ እናሪያ ወዘተረፈ አልነበሩም። ንጉሥም ሆነ የራሳቸው ፊደል አልነበራቸውም።

የሚያመልኩትም ለእባብ፣ ለውሃ፣ ለወርካ ወዘተረፈ ነበር።

የሃበርላንድ ብቸኛው እውነት የተመሠረተው በተረት ተረትና ይሆናል የፈጠራ መላምት ማስረጃነት የፈለቀው የጀርመን አሪያን ተብዬ ምርጥ ዘርያ ከመካከለኛው እሲያ ሂማሊያ ተራራማ ስፍራ መነሻ ምንጭ "ኡር ሃይማት" ፈልሶ ወደ ሰሜን ምዕራብ አውሮፓ ገባ ብለው ከሚያራግቡት ልበ ወለድ ጋራ በማመሳሰል የተዘጋጀው "<u>የጋላ ጎሣዎች መነሻ ምንጭ ጥንታዊ የባሌ ተራራማ ቦታ ነው</u>" የተሸኘው "አዲስ ታሪክ" በዘመናዊ የጋላ ልሂቃን እንደ መሐመድ ሐሰን አስፋ ጀለታ፣ መኩሪያ ቡልቻ፣ ወዘተረፈ በመሳሰሉት ሁሉ እንደ ገደል ማሚቶ ይስተጋብል።

በመጀመሪያ ሃበርላንድ ባሌን የመረጠበት ምክንያት ምንድ ናቸው?

1. በባሌ ደጋማ ገብስ ስልሚበቅልና ጋሎች ከመጀመሪያው ጀምሮ ከብት አርቢና የዶማ ግብርና ስለሚችሉ፣
2. የጋሎች የቀን መቁጠሪያ የወሩ መጀመሪያ ደገኞች እንደነበሩ ስለሚያረጋግጥ፣
3. ለደጋ አካባቢ ተስማሚ የቀንድ ከብትና ላተ ቀጭን ወይም ቾራት ረጅም በግ ስላላቸው፣
4. በቤት ውስጥ ምሰሶው የማምለኪያ ስፍራ መሆኑ፣
5. የአፈጣጠር አፈ ታሪካቸው፣ ባርጋሞ ማለትም ከባሕር ወዲያ፣ ማዶ

# <u>ባሌ የጋላ ጎሣዎች መነሻ ምንጭ አይደለም</u>

የሃበርላንድ የባሌ መነሻነት መላምትን ወድቅ የሚሆኑበት ሐቆች በዝርዝር፣

1. ከባሌ ደጋማ ስፍራ ይልቅ በሰሜን ኢትዮጵያ ጥቂት የጥንት ቅርስ የምግብ አመራረት ምርምር ግኝት ይገኛል። በአክሱም፣ በጣና ሐይቅ አጠገብ ነጭ ቤትና ላሊበላ የገብስ፣ የሽንብራ፣ የምስር፣ የከብትና የበግ አጥንት በጄ ደምብስኪ የተደርገው ጥናት ( T.Shaw: The Achoegy of Africa, Food, metals and towns ( London: 1993) pp.345-357 በሰሜንና መሃል አገር ከብት አርቢና ገበሬዎች ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ዘንጋዳ፣ ማሽላ፤ ወዘተረፈ አምራችነት ከ5000 ዓ.ዓ በፊት መኖራቸውን የኽረት (1982)፣ የብራንድት(1984)፣ የገራዚኦስ (1964) ጥናቶች ያረጋግጣሉ። በደዋሮ ጨርጨር ለጋ አዳ የድንጋይ ዘመን መሣሪያ እንጂ የእርሻ ሥራ መከናወኑ አልተረጋገጠም። በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ገብስና ስንዴ ዘርያን ያለመዱት የአማራ፣ የጋፋት ያገውና የጉራጌ ገበሬዎች ናቸው።

2. በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ እስከ ዛሬ በተደረገው ሳይንሳዊ ጥናት የበሬና የበግ ዘርያ ከእሲያ ወደ አፍሪቃ ከሁለት አቅጣጭያዎች ባለረጅምና አጭር ቀንድ፣ ሻኛየለሽና ሻኛማ
የበሬ ዘርያ እንደገቡ ነው። (Payne, W.J.A & Hodges (1977) Tropical cattle: origins, Breeds and breeding ) ባለሻኛ ዳልጋማ የበሬ ዘርያ በሕንድ ምድር ለማዳ ተደርጉ ወደ አፍሪቃ አህጉር ገብቷል። ኢትዮጵያ የልዩ ልዩ ሰብሎች ዘርያ መገኛ አገር ናት። የገብስ፣ የጤፍ፣ የስንዴ፣ የማሽላ፣ የሱፍ፣ የስናፍጭ፣ የእንሰት፣ የቡና ወዘተረፈ እነዚህን ሰብሎች ያለመዱት ዐማራዎች፣ አገዎች፣ ጉራጌዎች እንጂ ዘላን ጋሎች፣ ሹማሌዎችና አፋሮች አይደሉም። ከ1537 ዓ.ም በፊት የባሌ ክፍለ ሀገር ጥንት ነባር ነዋሪዎች አርጎባዎች፣ ዐማሮች፣ ሲዳማ-ሐድያዎች ሲሆኑ የከብትና የሰብል ዘርያ ያገኙትም ከሰሜንና መሐል ኢትዮጵያ ነዋሪዎች ነው። ለባሌ ደጋማ ሥፍራ ብቻ ተስማሚ ልዩ የቀንድ ከብት ዘርያ አልነበርም። በባሌ ደጋማ ስፍራ ከኤያላና ቀይ ቀበሮ በስተቀር የበሬ አውሬ ዘርያ (Bos primigenius opistonomous) የለም።

3. በሃበርላንድ ትረካ "የጋላ የዘመን መቆጠሪያ አዘገጃጀትና የወራቱ ስሞች አወጣጥ <u>በደጋ</u> አካባቢ እንደተደረገ ያመለክታል፣ ያመቱ መጀመሪያ ክረምት ከወጣ በኋላ ይጀምራል። ይህም ከሌሎቹ ደገኞች ኢትዮጵያውያን ድርጊት ጋራ ይስማማል።" ይላል። (ያው ገጽ 734) በተለይም የጋላ ቦረና እና ሌሎቹ ጎሣዎች ሁሉ ዓመት መጀመሪያው <u>በራ</u> ተብሎ እንደሚጠራ ተጠቅሷል። ነገር ግን ሃበርላንድ ይህ ቃል (በራ) በቀጥታ ከዐማርኛና ግእዝ ባራ፣ አባራ፣ በሪሃ፣ በርሀ መወሰዱን እንኳን አልጠቀሰም። ብራ ዝናም የሌለበት ቀንና ሌሊት ነው። በጋ ሐጋይ የድርቅ ወራት በባላገር ከመስከርም ጀምሮ እስከ ሰኔ በጋ ይባላል። ደግሞስ የይሁዲዎች ዘመን መለወጭያ እንደ አበሻና ጥንት ግብፃውያን በመስከረም ወር ክረምት ሲጠባ ነው። ታዲያ! ዕብራውያን ዘላኖች እንደ ጋሎች ደገኞች ይሆኑ? በርግጥም ሁሉም ማለትም አረቦች ጋሎች፣ ሱማሌዎች፣ አፋርና ቤጃዎች ዘላን ናቸው።

በምድረ ግብጽና ኢትዮጵያ ከዘመነ ፈርዖን ሥርዎ መንግሥት ጀምሮ ቀዳሚ የወርና የዓመት መዠመሪያ፤ ዘመን

መለወጭያ መስከረም ነው። ጥንት ግብጻውያንስ ከየትኛው ደጋማ ስፍራ መነጩ? በአጠቃላይ የዘመን መለወጭያ በመስከረም መጀመርና የወራት ስሞች የአንድን ነገድ መነሻ ስፍራ አያመለክትም። ስለሆነም ነው ጣሊያኑ ችሩሊ ስለ ጋሎች መነሻ አገር ምርምሩ ለወራት ስም አሰጣጥ ዋጋ ያልሰጠው።
የኢትዮጵያና የግብፅ የፀሐይና ጨረቃ ዘመን መቁጠሪይና የወራት ስያሜዎች ከግብርና ተግባር ጋራ በቀጥታ የተያያዙ ናቸው።

4. ስለ ምሰሶው (ኡቱባ) ማምለኪያነትና የታሪክ ሰንድነት በጋላ ጎሣዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በነባሩ ሕዝብ በሰባት ቤት ጉራጌ፣ በሃድያ፣ በትግሬ፣ በአገው፣ ባማራ ወዘተረፈ የዘመንመለወጭያ ቅዱስ ዩሐንስና የመስቀል ችቦ የሚለኮሰው፤ እንቁጣጣሽ የሚታሰረው በምሶሶ ላይ ነው። ምሶሶ እንዴት ሆኖ ነው ለጋላ ጎሣ የነባር ሕዝብነት ማስረጃ የሚሆነው?

5. የጋላ ጎሣዎች ከቀንድ ከብት ጋራ ከኢኮኖሚ ጠቀሜታ በይበልጥ ልዩ ስሜትና ባሕላዊ ትስስር ከሌሎች ጎሣዎች የበለጠ ነው ተብሎ በፈረንጅ የጎሣ ሊቅ ነን ባይ አወናባጅ ሁሉ ከመጠን በላይ ተጋኖ ተናፍሷል። ነገር ግን በምሥራቅ አፍሪቃ የመሳያ፣ የዲንቃ፣ የሂማ፣ የሀሬሮ ዘላን ጎሣዎች ስለከብት ያላቸው አስተሳሰብስ ለምን ይሸፈጣል? በዘላን መሳያ ነገድ ተውፌት የቀንድ ከብት እግዜር ለመጀመሪያው ማሳይ ማሳኒታ ከገነት ስማይ ያወረደለት ስለሆነ እንደራሱ አድርጎ ከብትን እንዲወድ ስለነገረው መሳያ ከብትን ከምንም ነገር አብልጦ ይወዳል።

6. የገዳ ሥርዓት ባፍሪቃ <u>የጋላ ጎሣ ብቻ</u> ልዩ መለያ ባሕል ተደርጎ ይነበነባል። ሀቁ ግን በእድሜና በፆታ መለያነት የሚመሠረት ኅብረተሰብ አወቃቀር የምሥራቅ አፍሪቃ ባንቱና አባያውያን ነገዶች ሁሉ አጠቃላይ አድረጃጀት ነው። ከሉዎችና ጁር በስተቀር ሁሉም በእድሜ ቡድን አድረጃጀት ለምሳሌ በመሰያ 15 ዓመት፤ በሙርሌ 6 ዓመት፣ በአኮሌ 10 ዓመት፣ በሱር፣ በናንዲ፣ በዲንቃ፣ በኪክዩ፣ በካሊንጅ ወዘተረፈ ሁሉ ይከናወን ነበር።
ስለምን የጎሣ ጥናት ተመራማሪ ተብዬ ስላዩች የገዳ ሥርዓት የአባያውያንና ባንቱ ነገዶች ፈጠራ መሆኑን ሸፈጡት?

7. በካማዊ ወይም ኩሻዊ ቋንቋዎች ምደባ ሽፉን ያውሮፓ ዘረኛ ከፋፋዩችና የጋላ ልሂቃን ጀሌዎቻቸው ብዙ ቀባጥረዋል። ካማዊነት ወይም ኩሻዊነት የነባር ሕዝብነት ማስረጃ እንደሆነ አስመስለው እጅግ በጣም አሳፋሪ ተረት ያነበንባሉ። በተለይም የዝንጆሮዋ ሉሲ አጽም በነሱ እጠራር ጭያልቱ የመጀመሪያዋ ኩሻዊ ኦሮሞ ናት ብለዋል። ምን ይህ ብቻ ኩሽ ኦሮሞ ያለም ሥልጣኔ መሥራች ነው ተብሎ ይቦተለካል። ቀልዱን ትተን ሐቁን ስናገናዝብ ካማዊ ወይም ከሻዊና ሰሜዊ ብለው ቋንቋዎችን ከብሉይ ኪዳን ዘፍጥረት ትረካ በመነሳት የከፋፈሉት አውሮፓውያን ናቸው።
በሃይማኖት ከለላ እስላም የሆኑት የአፍሪቃና እሲያ ነገዶች ሁሉ ለምሳሌ ሱማሌዎች፣ አፋሮች፣ ቤጃዎች፣ ቆቱዎች፣ ሃድያዎች፣ አደሬዎች፣ ሃውሳዎች፣ ሱዳኖች፣ የዋሱዋሂሊ ባንቱ ልዩ ልዩ ጎሣዎች በእሲያ የፓኪስታን ጎሣዎች፣ በሕንድ፣ ወዘተረፈ የዘር ግንዳቸውን <u>ከአረብ ሴማዊ</u> ከነቢዩ መሐመድ የትውልድ ሐረግ መቁጠራቸው ይታወቃል። ክርሲቲያን አበሻዎች ማለትም አገዎች፣ ዐማሮች፣ ትግሬዎች፣ ከፋዎች፣ ጉራጌዎች ወላሞች፣ ኩያራዎች፣ ጋሞዎች፣ የሞች አናሪያውያን ወዘተረፈ የዘር ግንዳቸውን ከአብርሃምና ከሣራ፣ ከዳዊትና ኢየሱስ ክርስቶስ ወገን፣ የአዲስ ኪዳን ምርጥ ሕዝብ መሆናቸውን ክብረ ነገሥት ይገልጻል።
ታዲያ! በኢትዩጵያ ካማዊና ሴማዊ የተባለው አጠራር ዘረኛ ፈረንጆች ከሰጡት ትርጉምና መከፋፈያ ስልታቸው፣ የጋላ ልሂቃን ስምተውና እንብበው ከሚ ያስተጋቡት ጋራ በጭራሽ አይስማማም።
ከኢትዩጵያ ሊቃውንት አንዱ አለቃ ታዩ ካማዊ ወይም ነገደ ኩሽ እና ሴማዊ ነገደ ዩቃጣን የተባሉት ሁሉም ከእሲያ ፍልሰው በቅደም ተከትል በባብኤል መንድብ በኩል አድርገው ወደ ኢትዩጵያ እንደገቡ ጽፈዋል። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስና እሲያ የሕዝብ ሁሉ መፈልቂያ መነሻ ምንጭ ናት ተብሎ ከሚተረከው ሃይማኖታዊ አስተያየት የመጣ ነው።
አለቃ ታዩ እንደጻፉት የኢትጵያ ሕዝብ ዋና ባላባት የሴም ዘርያዎች ስድስት ሲሆኑ እነሱም አገው፣ ዐማራ፣ በደው፣ ባቅላ፣ ትግሬ፣ አስገዴና ሕባባ ናቸው።
ጋፋቶች ከፊል ሴማዊና ከፊል ኩሻዊ ሲባሉ የጎንጋ ነገዶች ሁሉም ኩሻዊ ተብለዋል። አክሱም የነገደ ካም ዋና

መዲና፣ የግእዝ ቋንቋና ፊደልም የካም መታሰቢያ ይባላል (አስረስ የኔ ሰው 1943 ዓ.ም )
ነገደ አገው ሴማዊ ናቸው። ባሕላቸው፣ ዘራቸው ሆነ ቋንቋቸው ከዐማርኛና ግእዝ ቋንቋ ጋራ ይዛመዳል። ለምሳሌ የዐማርኛ ቋንቋ 70 በመቶ እጅ ከአገውኛ ጋራ ተዛማጅ ነው።
በስመ ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብነት አገውኛ ከምሥራቅ ቆላማ ኩሻዊ ወገን ከተመደቡት ጋልኛ፣ ስማሊኛ፣ አፋርኛ ወዘተረፈ ይልቅ በቀጥታ ሴማዊ ከተባለው ዐማርኛ ጋራ ያለው የዝምድና ደረጃ በጣም ከፍተኛ ሲሆን በአንጻሩ አገውኛ ከጋልኛ ሆነ ከሱማልኛ ጋራ ምንም ዝምድና የለውም።
ዘረኞች ዐማርኛና ግእዝ በኩሻዊ መሠረት ላይ የተቀረጹ ናቸው ብለው ዋሽተዋል። ያማርኛ ግሥ ከባለቤቱ መጨረሻ ላይ መሆኑ የኩሻዊና ኦሞዊ ቋንቋዎች ተጽዕኖ ነው፤ ዐማርኛ በዝኀቃ በ3ኛው ዕምዕተ ዓመት የተፈጠረ ነው ብለው ወሻክተዋል። ያውሮፓ ዘርኞች ለቅኝገዥ ተስፋፊነት እሳቦታቸው የብሪታኒያ ምሥራቅ ሕንንድ ንግድ ድርጅት ተቀጣሪዎች የፈጠሩት የሕንድ-አውሮፓ (Indo European ) የቋንቋና የዘር ቤተሰብነት ወገን የተደረጉት የሕንድኛ፣ የፋርስኛ፣ የቤንጎልኛ ቋንቋዎች ዐረፈተ ነገር ግንባታና ድምፅ አወጣጥ እንደ ዐማርኛ፣ አገውኛ፣ ትግርኛ ግሡ በስተመጨረሻ ላይ ነው።
ምነው ታዲያ! እነዚህ ቋንቋዎች ከአፍሪቃ አሲያ ቋንቋ ቤተስብ ወገን አልተመደቡም?
የግእዝን ቋንቋ እንበለ እፍረት ያርብኛ የቅርብ ዘመን ዘዬ እንድሆነ አስመስለው ጽፈዋል፡ ዐማርኛ እንደ አገውኛ ለረጅም ዘመናት የጽሑፍ ቋንቋ እንደ ገእዝ ባለመሆነቸው ብቻ የቅርብ ጊዜ ፍጥረት እንድሆኑ ተደርጎ የሚወራው ፍሬከርስኪ ነው።
ዐማርኛና ግእዝ ሁለት እሕትማማች እንጂ አባትና ልጅ ያለመሆናቸው እነ ዲልማንንና ሮዲጀር ያደረጉት ጥናት ያረጋግጣል። ጉራግኛም ቀዳሚ ሰማዊ እንጂ ያክሱማውያን ሠራዊት ጨዋ ስፋሪ ሠራዊት ቋንቋ አለመሆኑ ታውቋል። በአፍሪቃ እምብርት አባይ ሸለቆና በኢትዩጵያ አምባዎች በግብፅ ከዘመነ ፈርዓን ሥርዎ መንግሥት ምሥረታ አስቀድሞ በፑንት ምድር የኖረውና የሚኖረው የአበሻ አገው፣ ዐማራ፣ ጉራጌ፣ ጋፋት፣ ጎንጋ፣ እናሪያ፣ የም፣ ከፋ፣ ወዘተረፈ ሕዝብ ለመሆኑ እጅግ ሰፊ የሂሮግሊፍስ ጽሑፍ ሰንድ ይገኛል። የጥንት ግብፅ ፈርኦንና ሕዝብ የዘር ግንድ ከምደረ ፑንት ቅዱስ አገር ጠነጠር ነዋሪ ያበሻ ሕዝብ ወገን ነው። የፑንት አበሻዎችና የጥንት ግብፃውያን ከአንድ የቀይ ሕዝብ ዘርያ ወገን ነበሩ። ግብጻውያን አራት ዓይነት የሰው ዘር ነበሩዋቸው፣ እነሱም ቀይ፣ ጥቁር፣ ብጭያ፣ና ነጭ ናቸው። የጥንት ግብጻውያን ኩሽ ወይም ኩሳ ብለው የሚጠሩት ከፑንት ሀበሻ የቅመማቅመም ቅዱስ አገር ሕዝብ የተለየ ነው። ፑንት የሃበሻ አገር ፈርዕኖች በሙሉ መለኮታዊ ሥልጣን የተቀቡት ከአባይ ምንጭ መነሻ ነው ብለው ያምኑ ነበር። ዋዲ ሃልፋ ከተባለው ቦታ የሚገኘው ሰሌዳ ከግብፅ በስተደቡብ ያሉትን ልዩ ልዩ ነገዶች ስም ዝርዝር ለምሳሌ፣ ሽሚክ፣ ኩሣ፣ ሻት፣ ሶባት፣ አቀርቃን ወዘተረፈ የመሳሰሉትን ይጠቅሳል። በፑንት አበሻ ሀገር ከአንድ ሺሕ ሰባት መቶ ዓመተ ዓለም በፊት ከፍተኛ ሥልጣኔ እንደነበረ የሂሮግሎፊስ የጽሕፍ ሰሌዳ ያስረዳል። አበሻ ማለት በጥንት ግብፅ ቋንቋ የሥጦታ አባት ማለት ነው። ሌላው ያበሻ ትርጉም በዘንዶ የተመሰለው ጣዖት መጠሪያ ነው። አበሻ የተባለው መጠሪያ ከጥንት ግብፅ ፑንት አበሻ የቅመማቅመምና እግዜር አገር በቀጥታ የወረደ እንጂ ዘረኞችና አፈቀላጤዎቻቸው እንዳናፈሱትና እንደሚቀላምዱት ከአረቢያ ባሕረ ገብ ምድር ወደ ኢትዩጵያ ለተሰደዱ ዘላን ነገዶች መጠሪያ እይደለም። ሐበሻ ሕዝብ በኢትዩጵያ ምድር ከዘመን ፈርዓን 3800 ዓ.ም በፊት የነበረኛ ያለ ነው።
በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዩጵያን ሕዝብ ሴማዊና ካማዊ ብሎ መሸንሸን ፖለቲካዊ ስልት እንጅ ሥነ ተፈጥሯዊ መሠረት የለውም።ም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ዘመናዊው የሥነ ቋንቋ ጥናት እንዳረጋገጠው ሴማዊ ሕዝብና ቋንቋ በአረቢያ ከመገኘቱ በፊት በስሜን ምሥራቅ አፍሪቃ አፍሪቃ ከቅድመ ታሪክ ቢያንስ ከሁለት ሺህ ዓመታት ቅድሚያ እንዳለው የጄ ኸስደን (1978 ጥናት ያሳያል። የአፍሮ እሲያ ቋንቋ ቤተስብ መነሻ ምንጭ የኢትዩጵያ ስምጥ ሸለቆ ነው። በአረብ ባሕረ ሰላጤ በየመንና ኦማን በደቡብ ፋርስና ኢራቅ ጥንት ነዋሪዎች ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪ የጥቁር ሕዝብ ዘርያዎች ናቸው።

በኢትዩጵያ ከግራኝ አሕመድና ከተከተለው የጋላ ወረራ በፊት የባሌ ደጋማ ስፍራዎችን አጠቃሎ በምሥራቅ አሰክ ዝይላና በርበራ፣ በምዕራብ እስከ ዳሞት (ወለጋ) ቢዛንሞ ድረስ ባለው ምድር ነባር ነዋሪው ሴማው ቋንቋ ተናጋሪና አራሽ ልዩ ልዩ ነገዶች እስላምና ክርስቲያኖች እንዲሁም ለደስክና ለዲኖ አምላኪ አእዋሚዎች ነበሩ። የሸዋና የይፋት፣ ሱልጣናት፣ የሃድያ፣ የደዋሮ፣ የወጅ፣ የጉራጌ፣ የሃርላ፣ የአዳል ወላስማ ሱልጣናት ወዘተረፈ ሁሉም ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲሆኑ በአዳል ሱልጣናት ሥር በዘይላ የወደብ ከተማ ውስጥ እስከ ሃምሳ ቋንቋዎች ሲነገሩ ሁሉም የሚጻፉትም ባማርኛ ፊደል እንደነበር ታዋቂ የአረብ ሊቃውንት እነ ማቅሪዝ፣ ማሱዲ መዝግበውታል።

እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት ቅርብ ጊዜ ድረስ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ የነበሩት ልዩ ልዩ የሃድያ አላባ ማርቆ፣ የከምባታ፣ የእናሪያ ወዘተ ነገዶች በጋላ የሉባ ደፈጣ ተዋጊ ጦር ተወረው ከእልቂት የተረፉት ከርስታቸውና ንብረታቸው ተነቅለው ገባሮ የተባሉት ባሕላቸውና ሴማዊ ቋንቋቸው ለመለወጥ የተገደዱት። ቋንቋ በፍጹም ሥነ ሕይወታዊ ደንቢ ሳይሆን የማኅበራዊ መስተጋብር ውጤት ነው። ስለሆነም ነው በኢትዩጵያ ውስጥ በተለይም በሐረርጌ አርጎባዎች፣ በደቡብ ሸዋ ሃድያዎችና ሌሎች ነገዶች ቀድሞ "ሴማዊ" ተናጋሪዎች የነበሩት ሁሉ በቅርብ ዘመን "ኩሻዊ" ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑት።

ቋንቋና የቋንቆ ተዛማጅነት ለነባር ሕዝብነት ማስረጃ እንዳልሆኑ እየታወቀ መሀሐመድ ሀሰን ለጋላ ነገድ በኢትዩጵያ ግዛት ውስጥ በነባርነት ለመኖሩ ማስረጃ ብሎ የሚያቀርበው አንዱ የኩሻዊ ቋንቋ ቤተሰብነት ሲሆን፣ << ኦሮሞዎች የምሥራቅ ኩሻዊ ቋንቋ ቤተሰብ ወገን ሲሆኑ በኢትዩጵያ ግዛት ውስጥ ለሺህ ዓመታት መኖራቸው ይታወቃል። / The Oromo belong to the eastern Cushitic language speaking group of people which are known to have lived in the Ethiopian region for thousand years.>> (The Oromo of Ethiopia: A history 1570-1860, New York, PP.2-3)

ጋሊኛ ወይም ኦሮምኛ ምድቡ ከቆላማ ምሥራቅ ኩሻውያን (Lowland East Cushitic, LEC) ቋንቋዎች እንደ ሱማሊኛና፣ አፋርኛ ወገን ነው።

በኢትዩጵያ ግዛት ውስጥ ለሺህ ዘመናት የኖሩትና የሚኑሩት ከደጋማ ምሥራቅ ኩሻዊ (Highland Esat Cushitic, HEC) ቋንቋ ቤተስብ ውስጥ እንደ ሀድያ፣ ከምባታ ሲዳማ ጥምባሮ (አላባ) ጊዲኦ (ደራሳ) ቡርጂ (ባምባላ) ናቸው እንጅ የጋላ ጎሣዎች በጭራሽ አይደሉም። የሀድያ-ሲዳማ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከባሌ ተራራዎች በስተምዕራብ ጥንታዊ መኖሪያ አገራቸው በጋላ ሉባ ወራሪ በ1537 ዓ.ም ሲያዝባቸው ከፊሉ ሕዝብ ገባር ሆኖ በሞጋሳና ጉዲፈቻ የአሩሲ ጋላ ሆኖ ሲቀር ሲሦው ግን በሐድያነቱና ሲዳማነቱ የፀናው ወገን ከብቱን ይዞ በደቡብ ሸዋ በምድረ ጉራጌ እንደሰፈረ ብራውኬምፐር ያደረገው የመስክ ጥናት ያረጋግጣል። የሀድያ ነገድና ሱልጣናት ገራዶች በኢትዩጵያ ሰፊ የታሪክ ሰንድ ያላቸው፣ በአጤ ዓምደ ጽዩን ዘመነ መንግሥት የማዕከላዊ መንግሥት አካል ሆነው እንድቆዩ የተረጋገጠ ነው።

8. ፍጥረታችን ከውሃ ነው "ኡሜን ወለቡ ባቲ" የተባለው አፈታሪክ የጎሣ ሊቅ ተብዬዎች እንደሚያወሩት ያማራ ደብተሮች የነ አለቃ ታዬ ፈጠራ በጭራሽ ሳይሆን ጋላ ሁሉ ከባርጋሞ ማለትም ከባሕር ማዶ መጣን፣ ወጣን ብለው እንደሚተርኩ ላምበርትስ ባርቴስ (1983()፣ ጀምስ ብሩስ (1777) በኢትዮጵያ ቆይታው በጎጃም የሰፈሩ ሜጭያ ጋላዎችን ጠይቆ የመዘገበው፣ አይከ ሃበርላንድ ራሱ በሰበሰው ተረት << ሁሉም ጋሎች የጋራ ተውፌታዊ መነሻ ምንጭ አላቸው። የሚያምኑት የመጡት ከባርጋሞ ነው፣። የዚህም ትርጉም ከባሕር ወድያ፣ ከባሕ ማዶ ማለት ነው (All the Galla have a common mythical belive concerning their origin of the tribe: Thy belive that they came from a land called Bergamo, which can be translated beyond the sea.>> .( Galla-Südäthiopien 1963, p.772)

ይህ ተውፌት ሐበርላንድ ከባሌ ደጋማው ሥፍራ መኖሪያቸው በሕዝብ ቁጥር ጭመራ ምክንያት ወደቆላው ፈለሱ እያላ የፈጠረውን ተረት ይቃረናል። ከጋሎች የፈጠራ ተውፌት ጋራ አይስማማም። እራሳቸው ከባሕር ማዶ መጣን፣ ከባሕር ተፈጠርን እያሉ ከሚተርኩት ጋራ ይጻረራል። የባሌ ደጋማ ስፍራ በባሕር አልተከበበም።

ሁሉም የምሥራቅ ኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች አፋሮች፣ ሱማሌዎችና ጋሎች የቆላማ ስፍራ ነዋሪዎች ናቸው። ጋሎችም ከቆላማ ሥፍራ ተነስተው ወደ ለሙ የኢትዩጵያ ደጋማ አካባቢ በወረራ የፈለሱት። ለደጋማ አካባቢ ተስማሚ የቀንድ ከብት፣ና ባለቀጭን ላታማ በግ ያገኙትም ከነባሩ ያማራ፣ ያርጎባ፣ የጉራጌ፣ ጋፋት፣ ከምባታ፣ ሐድያ፣ ሕዝብ በዘረፉ ነው። ሰውን ሴት ወንድ ሳይለዩ በሉባ ደፈጣ ውጊያ ሲገድሉና ሲሰልቡ ነበር። የገበሬውን ሃብት የቀንድ ከብቱንና የጋማ ከብቱን እንዲሁም ፍየልና በጉን ከሸዋ፣ ከደዋሮ፣ ከፈጠጋር፣ ከጉራጌ፣ ከዳሞት፣፣ ከአንጎት፣ ከጎጃም፣ ከገንዝ ወዘተረፈ በብዛት እንደዘረፉት በትክክል ተመዝግቧል። ይህን ሐቅ ሽፍጦ ነው የጀርመን የሥነ ጎሣ እጥኝ ተብዬዎቹ የመስክ ጥናት በ20ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ መጀመሪያ አካባቢ ላይ ላይ አደርግን ብለው በአለፉት አራት መቶ ዓመታት ውስጥ የጋላ ጎሣ ማኅበረስብ በኢትዩጵያ ምድር በወራሪነት መጥቶ በየሰፈረበት አካባቢ ሁሉ ክፍተኛ ለውጥ ማድረጉ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ይህን ሥነ ተፈጥሮዊ የለውጥ ሂደት በመሸፈጥ ሃበርላንድ የጋላ ጎሣ አባ ባሕርይ ዜናሁ ለጋላን በጻፉበት ዘመን ከነበረው ባሕልና ልማድ ምንም ያህል አልተቀየረም ብሎ ዓይኑን በጨው አጥቦ የቀላመደው። የጋሎች መነሻ የባሌ ደጋማ ስፍራ ነው ብሎ ሲተርት የሱማሌዎችን ግን እንዲያ በደፈናው አሁን ከሠፈሩበት በስተሰሜን ነው እያለ ያወናብዳል። ሰሜን አያለ ሲወሻክት አረቢያ ይሁን ግብፅ ይሁን ወይም የሰሜን አውሮፓ አገር መነሻ ስፍራን ለይቶ ይህ ነው ብሎ አልተናገረም።

ፕሮፌስር ገብሬ ጉልቱ
የአፍሪቃ ታሪካና ሥነ ቅርስ ባለሙያ